# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል

## 43ኛ ሳምንት

## ፍልሰታ ለማርያም

**ዓላማ:**

- ስለእመቤታችን የመጨረሻ ቀናት እና የመታሰቢያዋን ጸሎት መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**

- "ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል።" ሉቃ. 1፣ 48

**ምንባብ**

- ስንክሳር።

**መግቢያ:**

- ከነሐሴ 1-15 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የምናስብበት ጾም እንጾማለን።
- ይሄም ሐዋርያት ከእመቤታችን ሞተ ዕርፍት በኂላ የጾሙት ነው።
- በዚህ መሠረትም በዛሬው ትምህርታችንም ስለ እመቤታችን ዕረፍት እና ሐዋርያት በዕረፍትዋ ተሰባስበው የተፈጸመውን ተዓምራት እንማራለን።

**ትምህርቱ**

- እመቤታችን ቅዲስት ድንግል ማርያም በተወለደች በ64 ዓመትዋ በልጅዋ በኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ተከባ አርፋለች።
- ሐዋርያቱም ከእነርሱ በመለየትዋ አዝነው ነበር። አይሁድ ይሄን ሲሠሙ ***"እንደ ልጅዋ ተነሥታ አረገች እንዳይሉን"*** ብለው ሥጋዋን ወስደው ለማቃጠል ፈለጉ።
- ከአይሁድ ታውፋንያ የሚሉት ጉልበተኛ መጥቶ እመቤታችን ያረፈችበትን አልጋ ገለበጠው።
- ነገር ግን የጌታ መልአክ እጁን ቆረጠው።እጆቹም ከትከሻው ተለይተው በአልጋው ላይ ቀሩ።
- ታውፍንያም በታላቅ ድጋጤና መደነቅ ወደ ሐዋርያት ዞሮ ይቅርታ ጠየቀ።እነርሱም እመቤታችንን እንዲለምን ነገሩት።
- እንዳሉትም ወደ እመቤታችን ዞሮ እያለቀሰ ለመናት።እመቤታችንም ቅዱስ ጴጥሮስ እጁን ወደ ክንዱ እንዲመልስለት ነገረችው፤ ወዲያውም ዳነ።ቅዱስ ጴጥሮስም ሄዶ የጌታችን ምሥክር እንዲሆን አስተማረው።
- እመቤታችን ካረፈች በኂላ ቅዱስ መልአክ የእመቤታችንን ሥጋ ወስዶ ከሕይወት ዛፍ በታች  አስቀመጠው ሐዋርያው ዮሐንስ ብቻ ይሄን አይቶ ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው።
- በዚህ ምክንያትም ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ እንደ ዮሐንስ ለማየት ለ14 ቀናት ጾሙ።
- ይህ የሐዋርያት ጾምም የእመቤታችን መታሠቢያ ጾም (ጾመ ፍልሰታ) ይባላል።
- ጌታችንም ጸሎታቸውን ተቀብሎ ሥጋዋን ሠጣቸው።

**ከዚህ ታሪክ የምንማረው**

- በክርስቶስ የሚያምኑ ምልክቶች ይከተሉቸዋል።ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ከጽንስቷ ጀምሮ ብዙ ተአምራት ፈጽማለች።
- እንደ ክርስቶስ እናትነተዋም ከትውልድ ሁሉ ትበልጣለች።እኛን ለማማለድም ወደ እግዚአብሔር የቀረበች ናት።ለዚህም ነው በወንጌል ***"እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሠግኑኛል"*** ሉቃ.1፣48 ያለችው።

**ጥያቄዎች:**

1.እመቤታችን ስታርፍ ስንት ዓመትዋ ነበር?
2. አይሁድ ሥጋዋን ለማቃጠል የፈለጉት ለምንድነው?
3.እመቤታችን ያረፈችበትን አልጋ የገለበጠው ሰው ምን ሆነ?
4. ይህ ሰው ሐዋርያትን ሲለምን ምን አሉት?
5. እመቤታችን ስታርፍ ሥጋዋን ማን ወሰደው? የት?
6. ቅዱሳን መላእክት ሥጋዋን ከወሰዱት በኂላ ሐዋርያት ስንት ቀን ጾሙ?
7. ይህ ጾም ምን ይባላል?

**ይቆየን።**